## በበዝውውር ጣቢያው የበለጠ ሪሳይክል (መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል)ማድረግ ይችላሉ!

በቤት ውስጥ እንደገና ጥቅም ላይ ሊያውሏቸው ከሚችሏቸው ዕቃዎች በተጨማሪ በ 16101 Frederick Road, Derwood, Maryland 20855 በሚገኘው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ሼዲ ግሮቭ የመፈተሻ ተቋም እና የዝውውር ጣቢያ ሌሎች ነገሮችን እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል ይችላሉ።

**የተቋሙ የስራ ሰዓቶች:**
ከሰኞ - ቅዳሜ: 7:00 am - 5:00 pm
እሁድ: 9:00 am - 5:00 pm

ተቀባይነት ስላላቸው ቁሳቁሶች የተሟላ ዝርዝር እና መመሪያዎች ለማግኘት **MontgomeryCountyMD.gov/RecycleRight** ን ይጎብኙ።

### በዝውውር ጣቢያው ተቀባይነት ያላቸው ቁሳቁሶች ምሳሌዎች

- አንቲፍሪዝ እና የሞተር ዘይት
- የከባድና ቀላል መኪና ጎማዎች
- አልባሳት፣ ጨርቃጨርቅ እና ጫማዎች
- ኮምፒዩተሮች፣ ቴሌቪዥኖች እና ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች
- ትላልቅ የብረት የቤት ውስጥ ዕቃዎች
- የምግብ ዘይት
- ፕሮፔን እና ሂሊየም ታንኮች
- የሚያገለግሉ የግንባታ ቁሳቁሶች
- በቤት ውስጥ የሚገኙ አደገኛ ቆሻሻ (HHW)
- የፍሎረሰንት አምፖሎች እና ቱቦዎች
- የዘይት ይዘት ያለው ቀለም
- ቀለም የሚያቀጥኑ እና የሚያሟሙ ኬሚካሎች
- አልካላይን እና ዳግም ሊሞሉ የሚችሉ ባትሪዎች
- የሜርኩሪ ቴርሞ ሜትሮች
- የማጽጃ ምርቶች
- ፀረ-ተባዮች እና አረም ማጥፊያዎች
- የፎቶግራፍ ኬሚካሎች
- ትርፍና የማይፈለጉ ነዳጆች: ለምሳሌ ቤንዚን

Montgomery County, Maryland
Department of Environmental Protection
Recycling and Resource Management Division
Waste Reduction and Recycling Section
2425 Reedie Drive, 4th Floor
Wheaton, Maryland 20902
MontgomeryCountyMD.gov/RecycleRight
በስልክ ቁጥር 311 ወይም 240-777-0311 ይደውሉ
TTY: MD Relay 711

ይህን መረጃ በሌላ አማራጭ መንገድ ለማግኘት በ 240-777-6486 ላይ ይደውሉ።

ይህ መረጃ እንደገና ጥቅም ላይ በዋለ እና እንደገና ጥቅም ላይ ሊውል በሚችል ወረቀት ላይ ታትሟል።

Amharic
rev 1/23

# ሪሳይክሊንግ በቀላሉ



## በአፓርታማዎ ወይም በኮንዶሚኒየም ቤትዎ ውስጥ

DEPARTMENT OF ENVIRONMENTAL PROTECTION
MONTGOMERY COUNTY • MARYLAND
TRRAC
Think Reduce and Recycle at Apartments and Condominiums

## መቀነስ እና መልሶ መጠቀም

በሚገዙበት፣ በሚሰሩበት እና በሚዝናኑበት ጊዜ የሚፈጠረውን እና የሚጣለውን የቆሻሻ መጠን የሚቀንሱባቸውን መንገዶች ይፈልጉ። ምን እንደሚገዙ፣ የት እንደሚገዙ፣ እንዴት እንደሚገዙ (እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ መያዣዎችን ይጠቀሙ!)፣ እንዴት በጥሩ ሁኔታ እንደሚጠቀሙበት እና በማይፈልጉበት ጊዜ ምን እንደሚያደርጉት በጥንቃቄ ያስተውሉ(ይለግሱ!) ። የተፈጥሮ ሀብቶችን መቆጠብ ብቻ ሳይሆን ገንዘብ ይቆጥባሉ እና የካውንቲዉን ቆሻሻን በመቀነስ እና እንደገና ጥቅም ላይ በማዋል ቆሻሻን ሙሉ በሙሉ የማስወገድ ግብ ለማሳካት አስተዋፅኦ ያደርጋሉ!

## ሪሳይክል

በሞንትጎመሪ ካውንቲ የተቀላቀሉ ቁሳቁሶችን፣ የተደባለቀ ወረቀት፣ ቁርጥራጭ ብረታብረት፣ የጓሮ ዕፅዋት ቁራጮች እና የገና ዛፎችን እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል የሁሉም ሰው ግዴታ ነው። በካውንቲው ውስጥ ያሉት እያንዳንዱ የብዙ ቤተሰብ መኖሪያ ስፍራዎች ለእነዚህ ቁሳቁሶች በቦታው ላይ የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ፕሮግራሞች ሊኖሩት ይገባል። በመኖሪያዎ ስፍራ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቁሳቁሶችን ለመሰብሰብ እና ለማጓጓዝ የሚሆኑ ለአፓርትመንት-የሚመጥኑ የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ይገኛሉ። ማስታወሻ: የፕላስቲክ ከረጢቶች፣ ፊልም ወይም የመጠቅለያ ላስቲኮች (shrink wrap) እንደገና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይበልጥ ቅርብ ወደሆኑ የአካባቢው የሸቀጣ ሸቀጥ/የግሮሰሪ መደብሮች ሊወሰዱ ይችላሉ። እነዚህ በመኖሪያ ቦታዎ የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ መያዣ ዕቃዎች/ኮንቴነር ውስጥ መቀመጥ የለባቸውም።

## ክፍተቶችን ይዝጉ!

በሚገዙበት ጊዜ እንደገና ጥቅም ላይ ከዋሉ ቁሳቁሶች የተሠሩ ወይም እንደገና ጥቅም ላይ በዋሉ ማሸጊያዎች የታሸጉ ዕቃዎችን ይግዙ። “እንደገና ጥቅም ላይ ከዋሉ ይዘቶች በተሰራ” የሚለውን ምልክት ይፈልጉ። እንደገና ጥቅም ላይ የዋሉ ምርቶችን ሲገዙ እንደገና ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶችን ፍላጎት በማሳደግ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋል መርሃግብርን ስኬታማ ለማድረግ ያግዛሉ።

## ሪሳይክል ማድረግ ለምን ያስፈልጋል?

ሁላችንም ሐብቶቻችንን በአግባቡ የመጠቀም ሃላፊነት አለብን። እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል ኃይልን ይቆጥባል፣ ውድ የተፈጥሮ ሐብቶችን ይቆጥባል፣ ብክለትን ይቀንሳል እንዲሁም ለካውንቲው የቆሻሻ ማስወገጃ ተቋማት የሚላከውን የቆሻሻ መጠን ይቀንሳል። እንደገና ጥቅም ላይ በማዋል ለንጹህ፣ ለጤናማ አካባቢ እና ለዘላቂ ኢኮኖሚ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። እናም፣**እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል** በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ሕግ ነው።

## ያውቁ ኖሯል...

- አንድ የአልሙኒየም ጣሳን እንደገና ጥቅም ላይ በማዋል የተቆጠበው ኃይል ቴሌቪዥንን ለሦስት ሰዓታት የሚያስጠቅም ኃይልን ይሰጣል። እንደገና ጥቅም ላይ ከዋለ አልሙኒየም የአሉሚኒየም ጣሳዎችን ማምረት አዲስ ማዕድንን በመጠቀም ከማምረት ይልቅ 95 በመቶ ያነሰን ኃይል ይጠቀማል።

- አንድ ቶን (2,000 ፓውንድ) ወረቀት እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል 17 ዛፎችን ያድናል። አብዛኛዎቹ የቁርስ ሲሪያል ካርቶኖች መቶ በመቶ እንደገና ጥቅም ላይ ከዋሉ ወረቀቶች የተሠሩ ናቸው።

- መስታወት እና እንደ ስቲል እና አልሙኒየም ያሉ ብረቶች በጭራሽ አያረጁም - እስካሁን እንደገና ጥቅም ላይ የዋሉትን ያህል ወደ አዳዲስ ምርቶች እንደገና ሊመረቱ ይችላሉ። መደበኛው ብርጭቆ እስከ 70 በመቶ እንደገና ጥቅም ላይ ከዋለ መስታወት የተሰራ ነው።

- ፕላስቲኮች የፔትሮሊየም ስሪት ናቸው፣ ስለሆነም እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል ዘይትን ይቆጥባል። ወደ መጫወቻ ስፍራ ቁሳቁሶች፣ ቲሸርቶች፣ የመኝታ ከረጢቶች፣ የፓርክ ወንበሮች፣ የጓሮ በረንዳ/ዴክ፣ የቤት ውጭ የመመገቢያ ጠረጴዛዎች፣ የጓሮ የቤት ዕቃዎች እና የእንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ማጠራቀሚያ እቃዎች ተቀይሮ ስራ ላይ መዋል ይችላል።




**ለህንጻው አስተዳዳሪ ይደውሉ ወይም MontgomeryCountyMD.gov/RecycleRight ን ይጎብኙ**

**ማህበራዊ ሚድያ ላይ ይከተሉን**
Facebook: MyGreenMontgomery
Twitter & Instagram: MyGreenMC
Flickr: DEP Montgomery County
Youtube: MontgomeryCountyDEP

# የበለጠ ሪሳይክል ያድርጉ። በትክክለኛ መንገድ ሪሳይክል ያድርጉ!

## የተደባለቁ ነገሮች



### የመስታወት ጠርሙሶች እና ብልቃጦች

- ጥርት ያለ፣ አረንጓዴ እና ቡናማ የምግብ እና የመጠጥ የመስታወት ጠርሙሶች እና ብልቃጦች

ምሳሌዎች: ለስላሳ መጠጥ፣ ቢራ፣ ጭማቂ እና የወይን ጠርሙሶች፤ ስፓጌቲ ሶስ፣ ማዮኔዝ እና የፒክል ብልቃጦች

### የፕላስቲክ ጠርሙሶች፣ ብርጭቆ፣ ትሪዎች እና ክዳኖች

- ፕላስቲክ ጠርሙሶች፣ መያዣዎች፣ ብልቃጦች፣ ገንዳዎች፣ መክደኛዎች እና ክዳኖች፣ ባልዲዎች እና የአበባ ማስቀመጫዎች።
- ፕላስቲክ የሆኑ ዘላቂነት ያላቸው እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የመያዣ እቃዎች እና ክዳኖች
- # 1 'PET' ክሌምሼል መያዣዎች፣ ትሪዎች፣ ዴሊ መያዣዎች፣ ዶም፣ ኩባያዎች እና ክዳኖች

ምሳሌዎች: ጭማቂ፣ ውሃ፣ ለስላሳ መጠጥ፣የምግብ ዘይት፣ የአትክልት ቅመም፣ ሻምፖ፣ የመጸዳጃ ቤት ማጽጃ፣ የማጽጃ ንጥረ ነገር መያዣ እቃ፤ እርጎ፣ ማዮኔዝ ፣ ኪቲ ሊትር እና አይስክሬም እቃ እና ክዳኖች፤ እና የፕላስቲክ የአበባ ማስቀመጫዎች

### የአሉሚኒየም እና የሁለት አይነት ብረት ጣሳዎች እና የፎይል ምርቶች

- ባዶ፣ ለአደጋ የማያጋልጡ የኤሮሶል ጣሳዎች
- የአሉሚኒየም ጣሳዎች እና የሁለት አይነት ብረት (ስቲል/ቲን) የምግብ እና የመጠጥ መያዣዎች
- የአሉሚኒየም ፎይል እና የፎይል ምርቶች

ምሳሌዎች: ሰርዲን፣ ሾርባ፣ አትክልት እና የቤት እንስሳት የምግብ ጣሳዎች፤ የአሉሚኒየም ፎይል፣ የፎይል ማብሰያ እቃ (እንደ ፓይ ሳህኖች እና ላዛኛ መስሪያ ያሉ) እና ከፎይል የተሰሩ አሙቆ መመገቢያ ትሪዎች፤ የማብሰያ ዘይት ስፕሬይ፣ ዲዮድራንት፣ የፀጉር ስፕሬይ እና የመላጫ ክሬም ጣሳዎች

**ማስታወሻ:** ክዳኖች እና መክደኛዎች እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፣ ግን በመጀመሪያ ከጠርሙሶች እና ከእቃ መያዣዎች ይለዩዋቸው፣ ያለቅልቁት። ፕላስቲክን፣ ብርጭቆን፣ አልሙኒየምን እና የብረት ቁሶችን እንደገና ጥቅም ላይ የማዋያ ማጠራቀሚያ ውስጥ ከማስቀመጥዎ በፊት ባዶ ያድርጉት።

## የተደባለቀ ወረቀት




- ንጹህ፣ ደረቅ ወረቀት
- የወተት/የጭማቂ ካርቶኖች፣ የጭማቂ እና የመጠጥ ሳጥኖች፣ የቀዘቀዙ የምግብ ሳጥኖች እና የአትክልት እና ፍራፍሬ ሳጥኖች
- ጋዜጦች እና የማስታወቂያ ወረቀቶች
- መጽሔቶች እና ካታሎጎች
- የካርቶን እና የወረቀት ሰሌዳ ሳጥኖች
- የማይፈለጉ ደብዳቤዎች፣ ደረሰኞች እና ፖስታዎች (ፕላስቲክ መስኮቶች ያላቸውን ጨምሮ)
- የተቆራረጠ ወረቀት (በወረቀት ከረጢት ውስጥ)
- ጠንካራና ስስ ሽፋን ያላቸው መፃህፍትእና የስልክ ማዉጫ መጽሃፍት
- የቢሮ/የኮምፒዩተር ወረቀት

## ቁርጥራጭ ብረቶች



- ብዙ የብረት ይዘት ያለውን ማንኛውም ነገር፣ የሚከተሉትን ጨምሮ: የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች (እንደ ብረት፣ ድስት፣ መጥበሻ፣ መብራት እና መስቀያ ያሉ)፣ መገልገያዎች (እንደ ማቀዝቀዣ/መጥበሻዎች ያሉ)፣ የብረት አልጋ ፍሬሞች፣ ካቢኔቶች፣ የቤት እቃዎች፣ አጥር፣ መሳሪያዎች እና ቧንቧዎች
- ቁርጥራጭ ብረት በቤትዎ ውስጥ እንዴት እንደሚሰበሰብ እና እንዴት እንደሚጣራ የህንጻዎትን አስተዳዳሪን ይጠይቁ። ቁርጥራጭ ብረትን በወረቀት ወይም በተቀላቀለ የእንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ማጠራቀሚያዎች ውስጥ አያስቀምጡ።
- አዲስ መሣሪያ ከገዙ መደብሩን የድሮውን መሣሪያ ማስወገድ እና እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚችሉ ይጠይቁ።

## የግቢ አትክልትና ዛፎች ቁራጮች እና የገና ዛፎች



- የታጨደ ሳር፣ ቅጠሎች እና አትክልት
- የተፈጥሮ (ጽድ) የገና ዛፍ
- ዳግም ጥቅም ላይ ከማዋልዎ በፊት ሁሉንም ጌጣጌጦች፣ መብራቶች፣ ቲንስል እና የአበባ ጉንጉን ያስወግዱ
- የገና ዛፎችን እንዴት እና መቼ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚችሉ የህንጻዎትን አስተዳዳሪን ይጠይቁ።

# እነዚህን ነገሮች እንዳይጨምሩ

- የተሰበረ ብርጭቆ፣ መስታወት ወይም መስኮቶች
- የመጠጥ ብርጭቆዎች፣ ኩባያዎች፣ ሳህኖች ወይም የማብሰያ ዕቃዎች
- ሴራሚኮች ወይም አምፑሎች
- የአውቶሞቲቭ መለዋወጫ ዕቃዎች
- እንደ ድስት፣ መጥበሻዎች ወይም የቤት ዕቃዎች ያሉ የብረት ዕቃዎች
- ስታይሮፎም™/ፖሊስትሪን ምርቶች (#6 ፕላስቲኮች)
- የፕላስቲክ መመገቢያ ዕቃዎች፣ ጎድጓዳ ሳህኖች ወይም ዝርግ ሳህኖች
- የሞተር ዘይት፣ አንቲፍሪዝ እና የፍሬን ፈሳሽን ጨምሮ የአውቶሞቲቭ የምርት መያዣ እቃዎች
- የፀረ-ተባይ መያዣ እቃዎች
- የፕላስቲክ ከረጢቶች፣ ፊልም እና የመጠቅለያ ላስቲኮች

---

- የፕላስቲክ ከረጢቶች፣ ፊልም እና የመጠቅለያ ላስቲኮች
- ስታይሮፎም™/ፖሊይስታይሬኔ ምርቶች (#6 ፕላስቲኮች)
- በምግብ (የፒዛ)፣ በቀለም ፣ በኬሚካሎች ወይም በኪቲ ሊትር የተበከለ ወረቀት / ካርቶን
- የስጦታ መጠቅለያ ወረቀት ፣ የወረቀት ፎጣዎች ፣ ናፕኪን ወይም ሶፍት

---

- የሞተር ብሎኮችን ጨምሮ የተሽከርካሪ ወይም የአውቶሞቲቭ ክፍሎች
- የቀለም ቆርቆሮዎች
- የኦክስጂን ወይም የፕሮፔን ታንኮች ወይም ሌሎች በውጥረት ውስጥ ያሉ ኮንቴይነሮች

---

- የስር መሸፈኛ ያላቸው ዛፎች
- በፕላስቲክ ከረጢቶች ውስጥ ያሉ ዛፎች